
NUR-
AFRICA
ACADEMY

## አማርኛ ቋንቋ 7ኛ ክፍል

## የዓ.ነገር ስልቶች

1. ሐተታዊ ዓ.ነገር፡- ይህ ዓ.ነገር አዎንታዊና አሉታዊ ዓ.ነገርን የያዘ ነው።

1.1 አዎንታዊ ዓ.ነገር፡- አዎንታዊ ሀሳብ የሚነገርበት ዓ.ነገር ነው።

- የተነገረውን ሀሳብ የሚደግፍ ነው።
- ዓ.ነገሩ መጨረሻ ላይ ወይም ግስ ላይ ያለው ቃል ደጋፊ ከሆነ ዓ.ነገሩ አዎንታዊ ዓ.ነገር ነው።

ምሳሌ፡- 1. ልጅቷ ት/ቤት መጣች። የተሰመረበት ቃል የዓነገሩን ሀሳብ ስለሚደግፍ አዎንታዊ ዓ.ነገር ነው።



2.2 <u>አሉታዊ ዓ.ነገር፡-</u> አሉታዊ ሃሳብ የሚነገርበት ዓ.ነገር ነው።

- ሃሳቡን አፍራሽ ነው።
- ዓ.ነገሩን መጨረሻ ላይ ወይም ግስ ላይ ያለው ቃል አፍራሽ ከሆነ ዓ.ነገሩ አሉታዊ ዓ.ነገር ነው።

<u>ምሳሌ፡-</u> 1. ልጅቷ ት/ቤት <u>አልመጣችም</u>። የተሰመረበት ቃል አፍራሽ ቃል ስለሆነ ዓ.ነገሩ አሉታዊ ዓ.ነገር ነው።

<u>2. መጠይቃዊ ዓ.ነገር፡-</u> ምላሽ የሚሹ ዓ.ነገሮች ናቸው።

- እነዚህ ዓ.ነገሮች በአብዛኛው በመጠይቃዊ ቃላት አማካኝነት ይመሰረታሉ።
- መጠይቃዊ ቃላት የሚባሉትም ማን፣ምን፣ለምን፣እንዴት፣መቼ፣የት የመሳሰሉት ናቸው።

<u>ምሳሌ፡-</u> 1. ንፁህ የመጠጥ ውሃ እንዴት ሊገኝ ይችላል?

3. ትዕዛዛዊ ዓ.ነገር፡- ትዕዛዛዊ መልዕክትን ለማስተላለፍ ይጠቅማል።

ምሳሌ፡- 1. እሱን መፅሀፍ አቀብለኝ።

2. በሩን ዝጋ!

4. አጋናኝ ዓ.ነገር፡- ትንሽ ነገርን አግዝፎ ያሳያል።

ምሳሌ፡- 1. ቤቱ ፈረስ ያስጋልባል!

## ጊዜ

- ጊዜ አንድ ድርጊት መቼ እንደተፈፀመ ወይም መቼ እንደሚፅም የሚገልፅ የግስ ባህሪይ ነው።
- ጊዜ በ3 ይከፈላል። እነሱም
  1. የአሁን ጊዜ
  2. የሃላፊ ጊዜ
  3. የትንቢት ጊዜ

- የአሁን ጊዜ፡- ዓ.ነገሩ በሚነገርበት ጊዜ የሚፈፀም ድርጊትን ይገልፃል።

ምሳሌ፡- 1. ኢክራም አሁን ደብዳቤ እየፃፈች ነው። ።

2. የሃላፊ ጊዜ፡- አንድ ድርጊት ተፈፅሞ ያለቀ መሆኑን ያመለክታል።

ምሳሌ፡- 1. አህመድ ከመቀሌ ትናንት መጣ።

3. የትንቢት ጊዜ፡- አንድ ድርጊት ገና ያልተፈፀመና ወደፊት የሚፈፅም መሆኑን ይገለፃል።

ምሳሌ፡- 1. ሰሚራ ነገ ዱባይ ትሄዳለች።